# የፌዴራል ሥርዓቱ ስኬትና የጥላሸት ቀቢዎቹ አፈ-ታሪክ

**ብሩክ ፈለቀ**

Tigrai Online – Dec. 23, 2013

ለዘመናት ጥቂት ፊውዳላዊና አምባገነናዊ ገዥዎችን ተጠቃሚ ያደረጉት ስርዓቶች ሀገራችንን በሁለንተናዊ መልኩ ክፉኛ ማድቀቃቸው የታሪካችን አንድ አካል መሆኑ አይካድም፡፡ በተለይም የጥቂት ወታደራዊ መኮንኖች ስብስብ የነበረው አምባገነናዊ የደርግ ሥርዓት እንደ መልካም የ"ስልጣን ዱላ ቅብብሎሽ" የህዝቡን ትግል በመቀማት ለ17 ዓመታት በሀገራችን ላይ ተጨማሪ ቁስል ፈጥሮባት ማለፉ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ከደርግ ውድቀት በኋላ ግን የተረጋጋች እና ህዝቦቿም በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድ የጋራ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት መስርተው እርስ በርሳቸው እየተከባበሩ በፈጠሩት ፌዴራላዊ ስርዓት የፈጣንና ተከታታይ ልማት ተቋዳሽ የሚሆኑበትን እንዲሁም ስር በመስደድ ላይ የሚገኝ ዴሞክራሲ ባህል እየተገነባባት ያለች ሀገርን ለመገንባት እጅግ የመረረ ትግልን በየደረጃው ጠይቋል፡፡ ታዲያ ይህን ሃቅ የማይቀበሉ ፅንፈኞች ትናንትም ነበሩ፤ዛሬም አሉ።

እርግጥ ሀገራችን እየተከተለች ባለችው ፌዴራላዊ ሥርዓት የተቀዳጀቻቸው ድሎች በርካታ ቢሆኑም ቅሉ፤ የቀድሞውን ስርዓት የሚናፍቁ ርዝራዦች እንዲሁም አስተማማኝነቱን በተግባር በማረጋገጥ ላይ የሚገኘውን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን በማጠልሸት ስራ ላይ የተጠመዱ ፅንፈኛ ሃይሎች ዛሬም ታሪካዊው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕለት በመጣ ቁጥር በቁጭት የማይወረውሩት የአሉባልታ ድንጋይ የለም። በቅድሚያ ለአንባቢዎቼ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ሀገራችን ሥርዓቱን ለመመስረት ፅንፈኞቹ ፈጥረውት ከተሻገረቻቸው ተግዳሮቶች መካከል ጥቂቶቹን በመዳሰስ፤ 'ፌዴራላዊ ስርዓቱን በቁጭት ማጥላላት የት ያደርስ ይሆን?' በሚል አንኳር ነጥብ ወደ ሰሞነኛው ተመሳሳይ አስገራሚ እሳቤያቸው እመለሳለሁ፡፡ መልካም ንባብ።...

...እንደሚታወቀው 1983 ዓ.ም አምባገነኑ የደርግ ሥርዓት ቢደመሰስም፣ ለሌላ ትግል የሚጋብዙ ፈታኝ የአስተሳሰብ ተግዳሮቶች መፈጠራቸው ግን አልቀረም፡፡ በወቅቱ በአንድ በኩል ተራማጅ የሆኑና ፌዴራሊዝም ለዘመናት ደም አፍሳሽ የሆነውን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ለመፍታት ፍቱን መድኃኒት መሆኑን ያመኑ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የመኖራቸው ያህል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ሁለት ፅንፍ ጫፍ ላይ የወጡ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ወገኖች ነበሩ።

ቀዳሚው በወቅቱ አስራ ሰባት የታጠቁ የብሔር ድርጅቶች የመኖራቸው ጉዳይ ነበር፡፡ እነዚህ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታን ባላገናዘበ መልኩ የችግሮች መፍትሄ መገንጣጠል ነው ብለው ያምኑ የነበሩና ለዚህም እንታገላለን የሚሉ ኃይሎች እንደነበሩ ያለፈው ድርሳናቸው ያወሳል፡፡ ሁለተኛው አዲሱን የሀገሪቱ መፍትሔ እና ፍቱን መድኃኒት የሆነውን የፌዴራሊዝም ሥርዓት ግንባታ እንደ መበታተን አደጋ በመመልከት ባረጀ እና ባፈጀ የአንድነት ስም የብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ መብት ብሎም መፈቃቀድን "በእኛ እናውቅልሃለን" የፖለቲካ እሽክርክሪት በማጦዝ ሀገሪቱን ወደ ማያባራ ቀውስ ውስጥ ለመክተት አልመው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ነበሩ፡፡

ታዲያ በወቅቱ እነዚህን ተግዳሮቶች በሰከነ ብስለት በመፍታት ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊት ሀገርን ለመመስረት ከፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር ከባድ ትግል ማካሄድ ግድ ብሎ እንደ ነበርና ውጤቱም በተራማጅ ሃይሎች አሸናፊነት እልባት እንደተሰጠው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በኋላም ቢሆን ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ አልነበረም። ሀገሪቱ ለመግለፅ በሚያስቸግር መልኩ ከባድ ፈተናዎች እንደገና ከፊት ለፊቷ ተደቀነባት፡፡ ከእነዚህ ፈተናዎች የላቀ ስፍራ የያዘው እና የሀገሪቱ ዋነኛ ጠላት የሆነው ድህነትን የመዋጋት ዘመቻ ነው፡፡ ይህ ጠላት ዓይኑን አፍጥጦ የመጣ ጋሬጣ ሆኖባታል፡፡ ታዲያ ይህ የጋራ ጠላት የሚደመስሰው በመንግስትና በሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተባበረ ክንድ በመሆኑ፤ ችግሩን ለመቅረፍ በቅድሚያ መንግስት የመሪነት ሚናውን በመወጣት ህዝቡን በአስተሳሰብ ደረጃ በድህነት ላይ ድል እንዲቀዳጅ የማድረግ ኃላፊነትን በሚገባ ለመውጣት ቆርጦ ወደ ትግበራ ለመግባት መዘጋጀቱ አይዘነጋም፡፡

በወቅቱ ‘ድህነትን የመታገል ታላቅ ጉዞ እንዴት ሊከናወን ይቻላል?፣ ይህን የጋራ ጠላት ተዋግቶ ለማሸነፍ መሰረታዊ የሚባሉ ቁልፍ ጉዳዮችስ ምንድናቸው?...ወዘተ’ የሚሉ ዋና ዋና ተግባራትን መለየት በእጅጉ ወሳኝ ነበር፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ግን በቅድሚያ የሀገሪቱ የበላይ ህግ የሆነው ህገ - መንግስትን ማፅደቅ ግድ አለ፡፡ ምንም እንኳን ህገ- መንግስቱን ለማፅደቅ መንግስት መድረኩን ክፍት ቢያደርገውም፤ አንዳንድ የቀድሞ ስርዓት ናፋቂዎችና የህዝቡን ስልጣን በአቋራጭ ለመንጠቅ ያሰፈሰፉ ፀረ-ሰላም ሃይሎች ግን ሁኔታውን በቀላሉ ሊቀበሉት አልቻሉም፡፡ ሆኖም በወቅቱ የነበረው የሽግግር መንግስት ስልጣን ከህዝብ የሚመነጭ መሆኑን ለእነዚህ ወገኖች ማስተማሩን አላቋረጠም፡፡ እናም ስልጣን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደሆነም በተደጋጋሚ በህዝቡ ዘንድ የማስረፅ ስራን አከናወነ፡፡ ይህን እያደረገ ባለበት ወቅት ግን ‘ሀገሪቱ ህገ - መንግስት ሊኖራት አይገባም እንዲሁም ብሔርን መሰረት ያደረገ ፌዴራላዊ ሥርዓት የምትገነባ ሀገር በምንም መልኩ ተጠቃሚ ልትሆን አትችልም’ የሚሉ ተቃራኒ አመለካከቶች ዋነኛ ፈተናዎች ሆነው ብቅ አሉ፡፡

ታዲያ እነዚህ ፈተናዎች ዴሞክራሲያዊ ምላሽ እየተሰጣቸው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በገዛ ፈቃዳቸው አምነው እና ተስማምተው ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም የኢፌዴሪ ህገ - መንግስትን አፀደቁ፡፡ ይህ ህገ - መንግስትም የቃል ኪዳናቸው ሰነድ በመሆን የኢትጵያ ህዝቦችን የዘመናት ጥያቄዎች የመለሰ መሆኑም ተረጋገጠ፡፡ ጥቂቶቹን ተግዳሮቶች ይህን ያህል ከተመለከትን ዘንዳ ድሎቹን ደግሞ እንዲህ እንቃኛቸዋለን።

ከዚህ በኋላ ሀገርን አዋርዶ፣ ህዝብን እያሸማቀቀ ለተመፅዋችነት የዳረገን ብሎም ለዘመናት እንደ ክት ዕቃ በዚህች ሀገር ተጎልቶ ከኖረውና ድህነት ከተሰኘው ጠላት ጋር ግልፅ ውጊያ ተከፈተ፡፡ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ከድህነት በላይ ጠላት እንደሌላቸውም አወቁ፡፡ ይህን ለመዋጋትም የሀገራችን ህዘቦች ከሊቅ እስከ ደቂቅ በመንግስት ውጤታማ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እየተመሩ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ዕድገት ማስመዝገብ ጀመሩ። ከድህነት አዙሪት ወደ ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት እሽክርክሪት።

ታዲያ ህገ -መንግስቱ ፀድቆ በሀገሪቱ የፌዴራል ሥርዓት ዕውን ከሆነ በኋላ፤ በህገ - መንግስቱ የተቀመጡት መሰረታዊ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዳዮች በሚገባ ምላሽ አግኝተዋል፡፡ ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር፣ የሚፈልጉትን ሃይማኖት በሰላማዊ መንገድ የማራመድ፣ በቋንቋቸው የመናገር እና የመጻፍ፣ ባህላቸውን እና እሴቶቻቸውን

በነጻነት የመግለፅ መብቶቻቸን ህገ- መንግስቱ በማያሻማ መልኩ አረጋግጦላቸዋል፡፡ እርግጥም የዘመናት የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል መንስኤም እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ነበር፡፡

ሆኖም 'የፌዴራሊዝም ሥርዓት በኢትዮጵያ ተግባራዊ ከሆነ፤ ሀገሪቱ ወደ አይሆኑ አዘቅት ውስጥ ትገባለች፣ የመበታተን አደጋ ይገጥማታል፣ ህዝቦቿ በየጎራው ተከፋፍለው እርስ በርሳቸው ይበላላሉ...ወዘተርፈ' በማለት በወቅቱ በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ የመገናኛ ብዙሃን የፖለቲካ ተንታኝ ሚርተኞች በተደጋጋሚ ፌዴራላዊ ስርዓታችን የማይጠቅመን አስመስለው ማራገባቸው አልቀረም፡፡ እርግጥ እነዚህ የመገናኛ ብዙሃንና ሚርተኞች በሀገሪቱ የተዘረጋው ፌዴራላዊ ሥርዓት ህዝቦቻችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ዘንግተውት አልነበረም— የቀድሞው ሥርዓት ናፋቂ ከሆኑት ፅንፈኛ ኃይሎች ጋር በመሰለፍ ማቀንቀኑን መርጠውት እንጂ፡፡ ዳሩ ግን እነርሱ ያሻቸውን ቢሉም መንግስትና ህዝቡ በውዠንብራቸው ሳይዘናጉ ብዝሃነታቸውን ውበታቸው በማድረግ አንድነታቸውን አጠናክረው፣ ለጋራ ዕድገት መረባረቡን ነው የመረጡት፡፡

ይህን ሃቅም ዶ/ር ሀሺም ቶውፊቅ በ1999 ዓ.ም "ስለ ኢፌዴሪ ህገ - መንግስት አንዳንድ ማብራሪያዎች" በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ላሪያ ዳይመንድ የተባለ የውጭ ፀሐፊን በመጥቀስ "ፌዴራሊዝም በማህበራዊ ምንነት ምክንያት የሚፈጠር ልዩነቶችን ለማቻቻል (አብሮ ለማራመድ) እና በማህበራዊ ምንነት ወይም በሌላ የማንነት ልዩነቶችን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን ለማስተንፈስ አግባብነት ያለው የፖለቲካ መሣሪያ ነው" በሚል ሁኔታ ምላሽ ሰጥተውበታል። ይህ አብሮነትም የጋራ ምጣኔ-ሃብታቸውን ለማሳደግ ሥርዓቱ የጎላ ሚና እንደሚጫወትም በማብራራት ጭምር፡፡

አዎ! ይህን ዕውነታ የተገነዘበው የሀገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስትም ህገ- መንግስቱን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በገዛ ፈቃዳቸው ተስማምተው እና ተማምነው እንዲያጸድቁት የተጫውተው ሚና በእጅጉ የላቀ ነው፡፡ ይህችን ሀገር ከአምባገነኑ የደርግ ሥርዓት አገዛዝ ያላቀቀው ኢህአዴግ መራሹ የሀገሪቱ ህዝቦች ትግል፤ ስልጣን በህዝብ እና በህዝብ ብቻ የሚረጋገጥ እንደሆነም የሚያምን በመሆኑ፣ በዚህ የሀገሪቱ የበላይ ህግ ህዝቦች የትግላቸው ባለቤት እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ በህይወት በነበሩበት ወቅት ስለ ፌዴራላዊ ሥርዓት አስመልክተው ያሉትን ሃቅ መጥቀስ ተገቢ ይመስለኛል—ያነሳሁት ሃሳብ ምሉዕ ይሆንልኝ ዘንድ። ታላቁ መሪያችን "ህገ - መንግስቱ የህዝቦቻችን የዘመናት ትግል ውጤት ነው፤ ይህን የህዝቦቻችንን የዘመናት ትግል ግምት ውስጥ በማስገባት ነው ህገ - መንግስቱ የተረቀቀው፡፡ የኢትዮጵያ ባህል ማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች ባህሎች ተደምረው የሚፈጥሩት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋ ማለት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ ተደምረው የሚፈጥሩት ጉዳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የህዝቦች ታሪክ ተደምሮ የሚፈጥረው ነገር ነው፡፡ ይህ ታሪክም በልዩነት የሚስተናገደው በፌዴራሊዝም ሥርዓት ነው" ብለው ነበር፡፡ እናም ለሀገሪቱ ብቸኛው አማራጭ ፌዴራላዊ ሥርዓትን መከተል እንደሆነም አስምረውበታል፡፡

እርግጥ ይህን የብልሁን መሪያችንን አባባል በተጨባጭ ዕውን ሲሆን አይተነዋል፡፡ ከእርሳቸው ህልፈተ-ህይወት በኋላም ቢሆን ስርዓቱ ፈሩን ሳይስት ቀጥሏል። ምንም እንኳን ህልፈታቸው በኋላ አንዳንድ ፅንፈኞች 'ሀገሪቱ ባልተረጋጋ ውስጣዊ የፖለቲካ ችግር ትናጋለች፣ ህዝቦቿ እርስ በርሳቸው ይባላሉ...ወዘተ' የሚሉ እሳቤዎችን ከተቃዋሚ ኃይሎች የዕብደት ትንታኔ እየሰጡ ቢዋትቱም፤ ይህን የሴራ አቋማቸውን ማንም እንዳልተጋራው በግልፅ ታይቷል፡፡ ምክንያቱም የፌዴራል ሥርዓቱ እነርሱ የሚሉትን አይነት በድንቡሽት የተገነባ ቤት ሳይሆን፤ በህዝቦች ፈቃድ ተረጋግጦ በጠንካራ

መሰረት ላይ የተገነባ በመሆኑ ነው። እናም ሥርዓቱን ሲመለከቱበት የነበረው መነፅር የተሳሳተ ዕውነታን ብቻ የሚያሳያቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል፡፡

እነዚህ ጽንፈኞች የታላቁ መሪያችን ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ድንገተኛ የዜና ዕረፍት ተከትሎ ያልቀባጠሩት የወሬ ዓይነት አልነበረም፡፡ የእነርሱ የወሬ ማራገቢያ የሆኑት ሚዲያዎችን በመጠቀምም፤ ‘ኢትዮጵያ ከድህረ መለስ በኋላ የተረጋጋ መንግስት አይኖራትም’ የሚል ትንቢት መሳይ ቅጥፈትን ማስታወስ ይቻላል፡፡ እርግጥ እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች በዜሮ ድምር የፖለቲካ ስሌት የሚመሩ በመሆናቸው ይጠቅመናል ብለው ካሰቡ ምንም ነገር ከማለት ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም፡፡ አሁን ከድህረ - መለስ በኋላ እነርሱ የተመኟት ኢትዮጵያ ‘አለች ወይ?’ ብለው እንኳን የማይጠይቁ የጨለማ ታንኳ ቀዛፊዎች ናቸው። አዎ! የእነርሱ በከሰረ የፖለቲካ እሳቤያቸው የሚያራምዱት ‘የሀገር ትበታተናለች’ ቀሽም ትንታኔ ከእነሱ ውጪ ማንንም ሊያሳምን አይችልም፡፡ ለዚህ አባባሌ ጥቂት አብነቶችን ላንሳ።

ሁላችንም እንደምናውቀው በክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ደንገተኛ ሞት ያልደነገጠ ኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያ ወዳጅ ህዝብ አልነበረም፡፡ ህዝቡ ለመሪው የነበረውን ጥልቅ ፍቅር በይፋ አስከሬናቸው ከውጭ ሀገር በመጣ ጊዜ የወቅቱ ዝናብ እና ብርድ ሳይበግረው ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ ቤተ- መንግስት ድረስ አጅቧል፡፡ ጥልቅ ሀዘኑንም ለሁለት ሳምንት ያህል ከአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን፤ በራሱ ፍቃድ ከክልሎችና ከውጭ ሀገር በመሰባሰብ ሃዘኑን ገልጿል፡፡ ፅንፈኞቹ ግን ይህን አይተው ሲያበቁ መለስን የሚተኩ እልፍ አዕላፍ መለሶች እንዳልፈጠሩ ሁሉ ሀገሪቱ አበቃላት ሲሉ ቢሳለቁም ህዝቡ ግን ጆሮውን ሊያውሳቸው አልፈቀደም፡፡

በእርግጥ የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ህልፈተ - ህይወት ጥልቅ ሃዘንን እና ድንጋጤን የፈጠረ ነበር፡፡ ነገር ግን ህዝቡ ከጫፍ እስከ ጫፍ ታላቁ መሪያችን በቀየሱልን የፌዴራላዊ ሥርዓት መንገድ ተከትለን አንድነታችን በማጠናከር በእልህ እና በወኔ ራዕይህን እናሳካለዋለን ብሏል፡፡ በርካታ የውጭ መገናኛ ብዙሃንም ከፅንፈኞቹ በተፃራሪ ህዝቡ ለመሪው ያደረገው የቀብር ሥነ-ሥርዓት አስገርሟቸው ‘ኢትዮጵያዊያን የሚወዳቸውን መሪያቸው በክብር ቀበሩ’ ሲሉ ዘግበዋል፡፡ የውጭ መገናኛ ብዙሃን እንዲህ ሲሉ የሀገራችን ተቃዋሚ ተብዬዎችና ፅንፈኛ ሃይሎች ግን የገዛ ሀገራቸውን ለብተና መመኘታቸው በህዝቡ ዘንድ ከትዝብት ውጪ ያተረፈላቸው አንዳችም ነገር የለም።

ያም ሆነ ይህ ግን፤ እንዳለፉት ሰባት ዙሮች ሁሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል መዲና በሆነችው በጅግጅጋ ከተማ አስተናጋጅነት ለስምንተኛ ጊዜ የተከበረው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን የፌዴራላዊ ስርዓታችንን ጥንካሬ ብሎም የህዝባችንን አንድነት በማጠናከሩ ረገድ የላቀ ሚና ተጫውቷል፡፡ “ህገ- መንግስታችን ለህዳሴያችን” የሚለውን መሪ ቃልም ተግባራዊ ለማድረግ ሕዝቦች ቃል ተግባብተዋል፡፡

ታዲያ ከትናንቱ ማንነታቸው ያልተማሩት ተቃዋሚ ተብዬዎችና ፅንፈኛ ሃይሎች ፌዴራላዊ ስርዓቱ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ ማሳያ የሆነውን የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልልን የትናንትና የዛሬ ልዩነትን እየተመለከቱም እንኳን ቢሆን፤ ዛሬም ስርዓቱን በባዶ ሜዳ ላይ ያለ አንዳች አስረጅ እንዲሁም በማህበረሰቦች ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን ጊዜያዊና ነባራዊ ሁነት በማጦዝ ከማጥላላት አልቦዘኑም። ታዲያ ይህ እኩይ ተግባራቸውም የሚያመላክተው ነገር፤ ልክ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ታሪክ ራሱን በመድገም እነዚህ ሃይሎች የስርዓቱን እመርታ ቁጭት በወለደው የተገለበጠ መነፅር እየተመለከቱ ለማደናገር እየሞከሩ መሆናቸውን ነው። እርግጥ የማደናገር ሙከራቸው ምንም ውጤት ሊያስገኝላቸው ባይችልም፤ መላው

የሀገራችን ህዝቦች በደማቸው የፃፉት ህገ-መንግስት የፀደቀበትና የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በመጣ ቁጥር የሚያላዝኑት የቁርጦ ቀጥልነት አታሞ ድለቃ ግን ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል።

ከስምንተኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን ጋር በተያያዘ ከቀረቡ አስገራሚ ዘገባዎች መካከል ከስያሜው ጋር የማይተዋወቀው "ፋክት" የተሰኘው መፅሔት በቅፅ 2፣ ቁጥር 23፣ ህዳር 2006 ዓመት ዕትሟ፤ ስያሜ በሌለው ዓምድ ስር ላይ ሃይለመስቀል በሸዋምየለህ የተባሉ ቋሚ አምደኛዋ አማካኝነት ያቀረበችው ፅሑፍ ይጠቀሳል—"ከብሔር ብሔረሰቦች ክብረ- በዓል ጀርባ" በሚል ርዕስ። አቶ ሃይለመስቀል በሸዋምየለህ "የከሸፈ ፌዴራሊዝም፣ ግራ የገባው ፓርቲ፣ የህወሓት ህገ-መንግስት እና ፈራሽ ህገ-መንግስት" በሚል አራት ንዑሳን ርዕሶች የከፋፈሉትና በስሜታዊነት 'እገሌ የተባለ አጥኚ እንዲህ ስላለ፣ ጉዳዮ ትክክል ነው' የሚል የምክንያትና የውጤት ትስስር የሌለውን ፅሑፋቸውን የተመለከተ ሰው፤ እርግጥም 'ሰውዬው በሸዋ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያም የሉም' ቢል አይፈረድበትም። ምክንያቱም ያነሷቸው ጉዳዮች እርሳቸውን ጨምሮ የራሳቸው ድብቅ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች የሚያቀነቅኑት አፈ-ታሪክ እንጂ፣ ሀገራችን ውስጥ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ፈፅሞ ስለማይመሳሰል ነው።

የፌዴራል ሥርዓቱ ስኬት ከሚያንገበግባቸው ግለሰቦች አንዱ መሆናቸውን ከፅሑፋቸው ሸውራራ ዕይታ በመነሳት ለመረዳት የማያዳግቱት እኚህ አፈ-ታሪክ ከታቢ ግለሰብ፤ የሀገራችን ፌዴራላዊ ስርዓት የከሸፈ መሆኑን በሚያስገርም ሁኔታ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ጥቃቅን ኑባሬያዊ ሰበዞችን እያጋነኑ በመምዘዝ በጭፍን ሊከራከሩ ይሞክራሉ። እናም በሚያስገርም ጨለምተኛ እሳቤያቸው ዓለም የመሰከረውን ዕድገት ያመጣው ፌዴራላዊ ስርዓት ከሽፏል ባይ ናቸው። ለዚህም በግጦሽ ቦታና በውሃ ምክንያት በአንዳንድ የሀገራችን ብሔረሰቦች መካከል ለዘመናት ሲከሰቱ የኖሩ ግጭቶች መኖራቸውን እንዲሁም አማርኛ ተናጋሪዎች ከጉራ ፈርዳና ከቤንሻልጉል ጉምዝ መባረራቸውን ...ወዘተ. በመጥቀስ የፌዴራል ስርዓቱ በእነዚህ ጉዳዮች ምክንያት የከሸፈ እንደሆነ በማስመሰል በድፍረት ፅፈዋል። መቼም 'ወቸው ጉድ!' እንጂ ሌላ ምን ይባላል?...

እኚህ በጨለማ ውስጥ የሌለን ነባራዊ ሁኔታ እየተነተኑ አፈ-ታሪክ የሚያንበለብሉ ግለሰብ በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ግጭት መቼም ቢሆን ሊጠፋ የማይችል ነባራዊ ሁኔታ መሆኑን አያውቁም ወይም ቢያውቁም ለመናገር የሚደፍሩ አይደሉም። ምክንያቱም ለእርሳቸው ጥላሸት የመቀባት ስራ ይህ ሃቅ ምንም ስለማይጠቅማቸው ነው። ሆኖም እንኳንስ የህዝቦች ንቃተ-ህሊና እየተገነባ እና ይበል የሚያሰኝ ደረጃ ላይ እየደረሰ ባለበት በእኛ ሀገር ውስጥ ቀርቶ በስልጣኔ እጅግ በዳበሩ ሌሎች ሀገሮች ውስጥም ቢሆን ግጭት መኖሩ አይቀርም። ሰው ከራሱ፣ በአቅራቢያው ካለውና ከተፈጥሮ ጋር መጋጨቱ አይቀሬ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በዓለማችን ላይ ያለው የተፈጥሮ ሃብት (Natural Resource) እጥረት ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ የተለየች አይደለችም—እንደ ማንኛውም የዓለማችን ክፍል የተፈጥሮ ሃብት እጥረት አለባት። እናም ግጭት ትናንትም ይሁን ዛሬ መኖሩ ያለና የሚኖር ጉዳይ ነው።

ሆኖም ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ካለፉት ጊዜያት ጋር ፈፅሞ በማይገናኝ መልኩ ለዚህ ነባራዊ ችግር ትኩረት ሰጥቶ በመስራቱ ሁኔታውን በመለወጥ ላይ ይገኛል። የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ያላቸውን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ እንዲጠቀሙና ከሌሎች ወንድም ህዝቦች ጋር በመተሳሰብ የጋራ ሃብታቸው እንዲሆን ማድረግ ችሏል። ዳሩ ግን ያለፉት ስርዓቶች በሀገራችን ህዝቦች ውስጥ ፈጥረውት ያለፉት የተዛቡ አመለካከቶች እንዲህ በቀላሉ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በቀላሉ የሚቀየሩ አይደሉም—ሂደትን፣ ጊዜንና የአስተሳሰብ ለውጥን ይጠይቃሉ። እናም ፀሐፊው ይህን ሃቅ ወደ ጎን ገሸሽ

አድርገው ስርዓቱን ጥላሸት ለመቀባት ካላቸው ፍላጎት ብቻ በመነሳት ‘የከሸፈ ፌዴራሊዝም’ መሆኑን ያለ አንዳች ሃፍረት ሊነግሩን ሞክረዋል። ግና እርሳቸው በሚያስገርም ሁኔታ እንደሚሉት የፌዴራል ስርዓቱ አልከሸፈም። ይልቁንም ስርዓቱ የሀገሪቱን ህዝቦች በአንድነት በማስተሳሰር ከሰሃራ በታች ጠንካራ ምጣኔ ሃብት መገንባት የቻለና ህዝቡንም በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ነው። ስለሆነም የሰውዬው ‘የክሽፈት ዓለም’ ምኞት በእሳቸውና በመሰሎቻቸው ምናብ ውስጥ እንጂ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስጥ የሌለ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ።

ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ይልቅ በፈረንጆችና የራሳቸው እኩይ አጀንዳ ባላቸውን ግለሰቦች አባባሎች የሚያምኑትና እነዚያን ሸውራራ ዕይታዎች እንደወረዱ የሚያቀርቧቸው አቶ ሃይለመስቀል፤ የአማርኛ ተናጋሪዎች ከጉራ ፈርዳና ከቤኒሻንጉል ክልል መባረራቸው የፌዴራል ስርዓቱ ክሽፈት ማሳያ መሆኑን ሲናገሩ ከዕውነታው በአያሌው ማፈንገጣቸውን ከመጤፍ አልቆጠሩትም። ዓይኔን ግንባር ያድርገው ብለው እየተከራከሩ መሆናቸውም ለፀሐፊ ተብዬው (የሰው አስተያየት ገልባጩ ብላቸው ሳይሻል አይቀርም) ምንም ማለት አይደለም። እውነታው ግን ሰውዬው እንዳሉት አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ከጉራ ፈርዳ ወረዳም ይሁን ከቤኒሻንጉል ክልል ሃላፊነት በማይሰማቸው ግለሰቦች አማካኝነት ተፈናቀሉትና ኋላ ላይ በመንግስት ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ የተደረጉት ወገኖች አማርኛ ተናጋሪዎች ብቻ አይደሉም። የኦሮሚኛና የሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎችም ይገኙበታል። ሰውዬው ይህን ዕውነታ እንኳን ለመጥቀስ አልደፈሩም። ዓላማቸው ህዝቦችን ከህዝቦች ጋር ለማጋጨት መሞከር ነውና።

ያም ሆነ ይህ ግን እዚህ ላይ ሀገራችን ውስጥ እየተገነባ ያለው ስርዓት ራሱን በራሱ እያረመና እያስተካከለ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። እንደሚታወቀው ማንኛውም ፌዴራላዊ ስርዓት በአንድ ጀምበር የተገነባ አይደለም። ተግዳሮቶች መኖራቸው አይቀርም። እናም በሂደቱ ውስጥ ጥቃቅን ስንክሳሮች ሊያጋጥሙት ይችላል። ዋናው ነገር እነዚህ ጊዜያዊ ችግሮች በብቃት እየተፈቱ የመሄዳቸው ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ በሀገራችን በመገንባት ላይ ያለው ፌዴራላዊ ስርዓት ለሚፈጠሩ ሁነቶች ወቅታዊና አስተማማኝ ምላሽ እየሰጠ ዛሬ ላይ የደረሰ ነው። በዚህም ሊፈጠሩ የሚችሉ አነስተኛ ኑባሬያዊ ተግዳሮቶችን በመፍታት ሁሉም የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በጋራ ተሳስበውና ተፈቃቅደው የሚኖሩበትን አስተማማኝ ስርዓት መፍጠር ተችሏል። ከዚህ ውጪ ፀሐፊው በጨለምተኛ እሳቤያቸው እንደለመዱት ‘እነ እገሌ እንዲህ ስለሆኑ ፌዴራላዊ ስርዓቱ ከሽፏል’ ማለታቸው ሰውዬው የሚያነሱት ሃሳብ እጥረት ያለባቸው መሆኑን ከማሳበቅ በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም። ነገርዬው ግን አስቂኝ ነው። እርሳቸው ስርዓቱን ቅዠት በወለደው ምናባቸው ካከሸፉት አሁን ያለው ስርዓት ከቶ ምን ይሆን?...“ዶሮ ብታልም ጥሬዋን” አሉ አባባ ተመስገን። መቼም ጭልጥ ባለ የጥላቻ መዘውር እየተመራ በእውር ድንብሩ የሚያስብ ሰው የሚበላውን ዳቦ ድንጋይ ነው ቢል የሚፈረድበት አይደለም—ማንኛውንም ነገር ከመካድ ወደ ኋላ የሚል አይደለምና።

ፀሐፊው ከንዑስ ርዕሳቸው ጋር ፈፅሞ የማይገናኝ ዘለፋንም በጥላሸት መቀቢያቸው ላይ አንስተዋል— ግራ የገባው ፓርቲ በሚል። ራሳቸው ግራ ተጋብተው ሌሎችን ግራ ለማጋባት የማሰኑት እኚሁ ጥቁር ቀለም ቀቢ ግለሰብ በዚህ ዙሪያ ያራመዱት ሸውራራ ሃሳብ ጠቅለል ተብሎ ሲታይ፤ ገዥው ፓርቲ የብሔር ብሔረሰቦችን ሉዓላዊ መብት ለፖለቲካ ፍጆታ እየተጠቀመበት እንደሆነ በተለመደው ‘እገሌ የተባለ ሰው እንዲህ ስላለ ትክክል ነው’ በሚል ጉንጭ አልፋ ክርክርን የያዘ ነው።...እርግጥ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ይህን የለየለት ውሸት በሚገባ ስለሚገነዘበው በጉዳዩ ላይ ብዙ ማለት ተገቢ አይመስለኝም። ይሁንና አንድ ዕውነታን ማንሳት እፈልጋለሁ—ገዥው ፓርቲ የታገለለትንና በህገ-መንግስቱ ውስጥ ተካትቶ ዛሬም ሆነ ነገ በፅናት የሚያምንበትን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማይገሰሱ መብቶች ላይ ከቶም ቢሆን ድርድር

የሌለው መሆኑን። እናም ሁላችንም እንደምናውቀው ፓርቲው ግራ የተጋቡት ጨለምተኛው ግለሰብና ቢጤዎቻቸው እንደሚያስወሩት ሳይሆን፤ የብሔረሰቦች መብት አያሌ የሀገራችን ህዝቦች ውድ ልጆች ቤዛ የሆኑለትና ለተግባራዊነቱ ህዝቦች በሙሉ የተረባረቡበት በመሆኑ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ገዥው ፓርቲም ይሁን የሀገራችን ህዝቦች ያላቸው አቋም መቼም ቢሆን ሊቀለበስ የሚችል አይደለም። እናም ፀሐፊ ተብዬ አሉባልታ ነዥውን ሰውዬ ‘ሲያምሮት ይቀራል’ ልላቸው እወዳለሁ።

አቶ ሃይለመስቀል የህገ-መንግስቱን ጥቂት አንቀፆችን ለአመል ያህል ይጥቀሱ እንጂ፤ ልክ እንደ ግንቦት ሰባት በጥላቻ የሚመለከቱት መሆኑን ‘የህወሓት ህገ-መንግስት’ በማለት የገለፁበት አባባል ሁነኛ አስረጅ ነው። ግንቦት ሰባት በትግራይ ህዝብና በመሪ ድርጅቱ ላይ ያለውን ጥላቻ ለመግለፅ ህገ-መንግስቱን ያልተገባ ስያሜ እንደሚሰጠው ሁሉ፤ እርሳቸውም ተመሳሳይ ንዑስ ርዕስን ለመጠቀም መሞከራቸው ግራ የሚያጋባ ነው። ምክንያቱም ትክክል ይሁንም አይሁን በፅሑፋቸው ውስጥ ‘የኢህአዴግ ህገ-መንግስት’ እያሉ ንዑስ ርዕሳቸው ግን በፅሑፋቸው ውስጥ በአንድም ቦታ ያልጠቀሱትን ‘የህወሓት ህገ-መንግስት’ ብለው መፃፋቸው ዓላማው ምን እንደሆነ ለማንም ግልፅ ስለማይሆን ነው። ያም ሆነ ይህ ግን ሀገራችን ውስጥ ያለው ህገ-መንግስት በራሱ በህገ-መንግስቱ ላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንጂ የአንድ ፓርቲ ባለመሆኑ ነው። ምንም እንኳን ሰውዬው ካላቸው ፍፁም ጥላቻ ያሻቸውን ለማለት ቢሞክሩም፤ ሃቁን የሚያውቀው የሀገራችን ህዝብ ግን ከትዝብት በስተቀር ሌላ ነገር ሊቸራቸው አይችልም። እንዲህ ዓይነት ቅጥ አምባሩ የጠፋና በቅጥፈት ላይ የተመሰረተ ጋዜጠኝነት ስለሌለ፤ እኔም በእርሳቸው ቦታ ሆኜ እንዳፍር ሆኛለሁ።

የሰውዬው ዘገባ እርስ በእርሱም የሚጋጭ ነው። በአንድ በኩል ‘አዛኝ ቅቤ አንጓች’ ተመስለው በውሸት ‘ገዥው ፓርቲ የብሔረሰቦችን ሉዓላዊ መብት ለፖለቲካ ፍጆታ ያውላል’ እያሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በእውነተኛው ማንነታቸው ‘የብሔር ብሔረሰቦችን ልዕልና አፍርሶ አዲስ ህገ-መንግስት ከማርቀቅ ውጪ ሌላ ምርጫ የለም’ በማለት የሚጋጩ ሃሳቦችን በማቅረብ ለማደናገር ሞክረዋል። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በህልም ዓለም ቅዠት ሲያፈርሱ የሚያድሩት የሀገራችንና የህዝቦቿ ጠላቶች፣ አሸባሪዎችና ፀረ-ሰላም ሃይሎች እንጂ፤ በህገ-መንግስቱ ያገኘውን መብት ተጠቅሞ በሰላማዊ ሁኔታ ስራውን የሚያከናውን ዜጋ አይመስለኝም። እርግጥ ሰውዬው እንደ ቢጤዎቻቸው በምናባቸው ህገ-መንግስቱን ሲያፈርሱ ቢያድሩ መብታቸው ነው። ዳሩ ግን ዜጎችን በሚዲያ ህገ-መንግስቱ ፈራሽ ነው ብሎ መቀስቀስ አግባብነት ያለው አይመስለኝም። ከሀገሪቱ የመረጃ ነፃነትና የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ጋርም መላተም አሊያም ህግን አለማክበር ይመስለኛል።

ያም ሆነ ይህ ግን እርሳቸውና ተመሳሳይ አቋም ያላቸው የውስጥና የውጭ ሃይሎች እንደሚመኙት፤ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተስማምተው ያፀደቁትና የሉዓላዊ ስልጣናቸው ምንጭ የሆነው ህገ-መንግስት እነዚሁ ህዝቦች እስካሉ ድረስ ፈራሽ የሚሆንበት ምንም ዓይነት ዕድል አለመኖሩን በሰከነ አዕምሮ ማገናዘብ ያስፈልጋል። እናም ብልህ የሆነ ሰው ሀገር ውስጥ ሆኖ የእነዚህን ህዝቦች ሉዓላዊ መብት በህልምም ቢሆን ለመጋፋት መሞከር ትርፉ ከህገ-መንግስቱና ከባለቤቶቹ ጋር በይፋ መላተም መሆኑን ያውቃል። ውጤቱም ፈራሽ ሃሳብን በምድረ-በዳ ላይ አቀንቅኖ ተተፍቶ መጣልን የሚያስከትል መሆኑም ጭምር።

በጥቅሉ ምንም እንኳን ፌዴራላዊ ስርዓቱን በደንብ ያተረዱና የራሳቸውን ህቡዕ ዓላማ ለማሳካት እንደሚጥሩት እንደ ፀሐፊው ተብዬ ዓይነት ፅንፈኞች ትናንት ሲፈጥሩት እንደነበሩት ተግዳሮቶች ሁሉ ዛሬም ያሻቸውን ቢሉም፤ ሥርዓቱ ግን ራሱን በራሱ እያረመ ለዛሬው የህዝቦች መፈቃቀድና አንድነት ያበቃን ብሎም ከመበታተን ይልቅ በዕድገት ማማ ላይ

እንድንወጣና ባለ ድል እንድንሆን ያደረገን መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። አሊያ ግን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል በመጣ ቁጥር ዕውነትን በጨለምተኝነት መሐረብ ሸፍኖ በቁጭት ማላዘንና ፌዴራላዊ ስርዓቱን ጥላሸት ለመቀባት መሞከር፤ በድብቅ ፖለቲካዊ አጀንዳ የህዝቦችን ስኬት እያጣጣሉና በሃሳብም ቢሆን ሉዓላዊ ስልጣናቸውን እየገፈፉ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን እየናፈቁ ከመቆዘም በስተቀር የሚያስገኘው ምንም ዓይነት ፋይዳ እንደሌለ መረዳት ተገቢ ነው።